# የሰፊው ሕዝብ ድምፅ

ለሰፊው ሕዝብ —ወዝአደር፡ገበሬ፡ነጋዴ፡ወታደር፡ምሁር—
መብትና ጥቅም የሚታገል ጋዜጣ

የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ይቅደም፡፡

ቁጥር 28 ቀን 22/10/67


## አብዮቱ እንዲገፋ

አገራችን እጅግ ከፍተኛ የሆነ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ከገባች እነሆ አመት ተኩል ሊሆናት ነው፡፡በዚህ አጭር ጊዜ ውስጥ ሰፊው የኢትዮጵያ ~~ሕዝብ~~ ለዘመናት የማይገኙ ጠቃሚ ትምህርቶችን በትግሉ ውስጥ ቀስሟል፡፡እጅግ መራራና ረዥም ትግል ገና ወደፊት ቢጠብቀንም ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት የወደፊት እድል ከፀሃይ ደርቶ የሚታይበት ወቅት ነው፡፡ከዚህ ሁኔታ ተነስተን አብዮቱ ወደፊት የሚገፋበትን ዘዴ መመልከትና ማመልከት የተራማጆች ሁሉ ግዴታ ነው ብለን እናምናለን፡፡

ዛሬ በ1967 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ተራማጆች ምን ምን አጣዳፊ ተግባሮች እንዳሉብን ለማየት በቀድሚያ አገራችን በታሪክ እርምጃ ጉዳና ሳይ የት እንደደረሰች ባጠቃላይ መጠቆም ተገቢ ነው፡፡በዚህ ጉዳና ላይ የምንገኝበትን ምእራፍ ለይተን ካላወቅን የመደቦችን አሰላለፍ መመልከትና ወዳጅን ከጠላት ለይቶ አብዮቱን ወደፊት ማራመድ አይቻልም፡፡

ኢትዮጵያ በአሁኑ ወቅት ከፊል ፊውዳላዊ ከፊል እጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ የተጫናት፤የሕዝቦችዋ ደህንነት፡ነፃነት፡እርምጃ... በነዚህ ጥንድ ጠላቶች ታፍና የተያዘባት አገር ነች፡፡በያዝነው ዘመን እንደኢትዮጵያ ባሉት አገሮች የሚደረገውና ሊደረግ የሚችለው አብዮት በወዝአደሩ መደብ የሚመራው አዲሱ ዲሞክራቲክ አብዮት ነው፡፡ይህ አብዮት ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ከምድረ ኢትዮጵያ ጠፍተው/ተደምስሰው/ አዲሱ ዲሞክራቲክ ስርአት የሚመሰረትበት፡ለሶሻሊስት ስርአት መንገድ የሚጠረግበት፡የአለም ሶሻሊስት አብዮት የማይነጠል አካል የሆነ አብዮት ነው፡፡

እንግዲህ ወደዚህ አብዮታዊ ግብ በመጓዝ ላይ እያለን ጨባጩን የኢትዮጵያ ሁኔታ በምንመለከትበት ጊዜ ሁኔታው እጅግ የተወሳሰበ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡የአገሪቱን ሁኔታ ከመደቦች አሰላለፍ አንፃር ብናየው ይህ የተወሳሰበ መልክ ቁልጭ ብሎ ይታያል፡፡በአንድ በኩል የዚህ አብዮት ደጋፊዎች ሊሆኑ የሚችሉት ሃይሎች በሙሉ በትብብር ሊሰለፉ አልቻሉም፡፡አጋዥ ሊሆኑ የሚችሉት አብዛኛው ንኡስ ከበርቴና ኢምንት ሃይል ብትኖረውም ከሕዝቡ ጎን መሰለፍ የሚችለው የብሄራዊ ከበርቴው ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ክንፍ ጨርሰው ከአድሃሪያቹ መደቦች ጋር ተደባልቀው ይገኛሉ፡፡ይህም በተለይ ደግሞ በከተሞች የአብዮቱን ሃይሎች አዳክሞ የፀረአብዮቱን ሰፈር አዳብሮታል፡፡በሌላ በኩል ደግሞ ቁርጠኛ የሆኑት የአብዮቱ ደጋፊዎች /ወዝአደሩና ሌሎችም አብዮታዊ የህብረተሰብ ክፍሎች.../ ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸው ታፍነው መደራጀት ባለመቻላቸው አብዮቱ በተለይ በከተሞች ደረቱን ለጠላቶቹ አጋፍጦ የሰጠበት አስጊ ሁኔታ አለ፡፡ከዚህም በተጨማሪ ከቀደሞው አገዛዝም ጋር ሆነ ዛሬ ከሚፍጨረጨሩት አድሃሪዎች ጋር በጥቅም በመያያዝ አብዮቱ ላይ ከማሴር በማይታክቱት አሜሪካኖች ላይ ቁርጥ ያለ ፀረኢምፔሪያሊስት አቋም በመንግስቱ አልተወሰደም፡፡እንዲያውም ሰፊው ሕዝብ ተገቢ የሆነ ፀረኢምፔሪያሊስት ትምህርት ቀስሞ ለብሄራዊ ነፃነቱ እንዳይታገል የአሜሪካን ኢምፔሪያሊስቶች ስም በምንም አይነት በክፉ እንዳይነሳ ተከልክሎአል፡፡

ባጭሩ፡የአብዮቱ ደጋፊዎች በወጉ አልተሰበሰቡም፤በወጉ አልተደራጁም፡፡ወላዋይ መደቦችና የህብረተሰቡ ክፍሎች ጨርሰው ከጠላት ተደባልቀዋል፡፡የአብዮቱ ጠላቶች መበተን መዳከም ሲገባቸው እየተደራጁና እየተጠናከሩ በመሄድ ላይ ናቸው፡፡አጠቃላይ ስእሉ ይህ ቢሆንም ጠጋ ብሎ ለሚመለከት ሰው በባላገርና በከተማ ፈጽሞ የተለያዩ ሁኔታዎች ይታያሉ፡፡ባላገሩ እነዚህን እንቅፋቶች በሃይልና በትግል እየተወጣ ዛሬ ገጠሪቱ ኢትዮጵያ/በተለይ በደቡብና በምስራቅ/ በአብዮታዊ ማእበል በመጥለቅለቅ ላይ ትገኛለች፡፡በተሰበጣጠሩ ምክንያቶች፡በተለይም በዲሞክራሲ መብቶች መታፈንና በመንግስቱ አድሃሪ ተጽእኖ የተነሳ በከተማ አብዮቱ እነዚህን እንቅፋቶች ለመወጣት

የገጠሩን ኃይል ፍጥነት አያሳይም::ይህ የተዛባ ሁኔታ በባላገር የተራወጡትን አድሃሪ ሃይሎች ከተሞች ፋታ እንዲሰጡአቸውና የአድሃሪ ሰራቸው መጠንሰሻ መድረኮች እንዲሆኑ አድርጓቸዋል::

ይህ ከሆነ በአሁኑ ወቀት የተራማጆች ጥረት በሁለት አቅጣጫዎች መካሄድ አለበት::በባላገሩ ተራማጆች ሃይላቸውን አስተባብረው አብዮታዊው ማእበል በምንም አይነት ገብ እንዳይል:እንዲቀጥል:አቅጣጫ እያሳዩ መታገል አለባቸው::በከተሞች ደግሞ የአድሃሪዎች ሰራ የሚከሸፍበትን ሁኔታ እያጠኑ በዚሁ አቅጣጫ በህብረት መታገል አለባቸው::

××××

I

በገጠር በኩል ኢትዮጵያ ዛሬ ለአብዮታዊ ትግል እጅግ ምቹ ምድር ሆናለች::ለብዙ ዘመናት ቦግ እልም እያለ ሲካሄድ የነበረው የተበዘባዥ ገበሬዎች ትግል ዛሬ በአብዮታዊ ማእበል አገሪቱን በማጥለቅለቅ ላይ ይገኛል::በተለይ የገጠርን መሬት የሕዝብ ለማድረግ የወጣው አዋጅ በአገሪቱ ያለውን የመደቦች አሰላለፍ የጠራና ቁርጥ ያለ መልክ ሰጥቶታል::ይህ አዋጅ የመደቦችን ትግል ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ አከርርትና አፋፍሞት እናያለን::ከዚህ አዋጅ በሂላ መሬት ከፍ ብትል ሰማይ ዝቅ ቢል ኢትዮጵያ የቀድሞይቱ ኢትዮጵያ አትሆንም::የየካቲት 25 አዋጅ ለኢትዮጵያ አብዮት አዲስ የህይወት እስትንፋስና የተጣራ የትግል አሳማ ሰጥቶታል::በኢትዮጵያ ገበሬዎች ልብ ግሩን ሳይመታ በምንም አይነት የማይጠፋ አብዮታዊ ቋያ ቀሰቀሰአል::

ይህንን አዋጅ ሙሉ በሙሉ ከስራ ላይ ለማዋል የሚደረገው ተጋድሎ ከኢትዮጵያ ምድር ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይምጥማጣቸው ሳይጠፋና ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ሳይቋቋም በምንም አይነት ገብ አይልም::በኛ እምነት ይህንን አዋጅ ከስራ ላይ ለማዋል ዛሬ መሬት ላራሹ በሚለው መፈክር ስር የተሰለፈው በሚልዮን የሚቆጠረው ገበሬ ቀስበቀስ በትግሉ ውስጥና ለትግሉ መቀጠል ሲል ነፃነት ላራሹ በሚለው መፈክር ስር የግድ መሰለፍ ይኖርበታል::ይህ 'ነፃነት ላራሹ' የሚለው መፈክር ደግሞ ሌላ ምንም ነገር ሳይሆን የኢትዮጵያ አርሶአደር 'መሬት ላራሹን' የሚፃረሩትን የቀድሞ ስርአት የመንግስት አውታሮች ሰባብሮና ደምስሶ በትግሉ ውስጥ የራሱን ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ የሚመሰርትበት መሳሪያ ነው::

የኢትዮጵያ ተራማጆች ከዚህ በፊት 'መሬት ላራሹ' የሚለውን መፈክር በግንባር ቀደምነት አንስተው ለሰፊው ገበሬ የትግል አቅጣጫ አሳይተዋል::ከእንግዲህ ደግሞ መሬት ያለነፃነት እርም መሆኑን ለአራሹ ገበሬ በቅድሚያ ማመልከትና በዚህ ነፃነት ደግሞ የአድሃሪውን ስርአት የመንግስት አውታሮች ደምስሶ የራሱን አገዛዝ ለመመስረት መታገል እንዳለበት ከትግሉ ተዋህደው ሊያስተምሩት ይገባል::

ይህ እንዴት እንደሚሆን ለመረዳት ከአዋጁ በተጨማሪ ይህንን አብዮታዊ ማእበል ለማስነሳት የረዱትን ነገሮች መመልከት ያስፈልጋል::በገጠር ዛሬ ይህንን አብዮታዊ ሁኔታ አዋጁ ብቻውን አልፈጠረውም::በቅድሚያ በባላገር የዘማቾች መገኘት የፈጠረው አብዮታዊ 'ዳይናሚክስ' መታየት አለበት::ከአስር አመታት በፊት ጀምሮ 'መሬት ላራሹ' በሚል መፈክር ሲሰዉ:ሲገረፉ:ሲታሰር:ሲሰቃይ የነበረው ወጣቱ የኢትዮጵያ ትውልድ ዛሬ በግንባር ቀደም ዘማቾች አማካኝነት ከድሃው ገበሬ ተዋህደአል::በአሁኑ ጊዜ የዘማቾች ከገበሬው ጉን መገኘት የፈጠረውን አብዮታዊ ማእበል ስንመለከት ይህ አዋጅ የወጣት ተማሪዎች የቀሰቀሳና የማደራጀት ተጋድሎ ባይጨመርበት ኖሮ አሁን ከምንገኝበት ከፍተኛ ደረጃ ምን ያህል ወደሃላ እንቀር እንደነበር ለመገመት አያዳግትም::ከነዚህ አብዮታዊ ዘማቾች ጉንም ተራማጅ የመሬት ይዞታ ሰራተኞች:እንደዚሁም አንዳንድ የሕዝቡን ወገን ያቀፉ ተራማጅ አስተዳዳሪዎች መኖራቸው አብዮታዊውን ማእበል ለመፍጠር የረዳ መሆኑን የሚጠራጠር የለም::

የነዚህ ልዩ ልዩ ሁኔታዎች ህብረት የፈጠረው አብዮታዊ ማእበል ተጠራቅሞና ተቀነባብሮ መልክ የሚያገኘው በገበሬዎች ማህበር አማካኝነት ነው::የገበሬዎች ማህበራትን ጉዳይ በሁለት

አገፀር መመለከት ያስፈልጋል::ማህበሮቹ የተቋቋሙት አዋጁን በስራ ላይ ለማዋል ሲሆን መደባዊ ይዘታቸውና /የቀድሞ ከፍተኛ ባለርስቶች አይገቡባቸውም/ አላማቸው የፊውዳል ኢትዮጵያ መደምሰሻ መሳሪያ ያደርጋቸዋል::እነዚህ ማህበራት እንደተራ 'የሞያ ማህበራት' መታየት የለባቸውም:: ባለው ስርአት ውስጥ የጢሰኛውን የኑሮ ሁኔታ ለማሻሻል ሳይሆን ጢሰኝነትን ጠርሶ ለማጥፋት የሚታገሉ አብዮታዊ አካላት ናቸው::እነዚህን ማህበራት የፊውዳሊዝም መደምሰሻ መሳሪያዎች ብቻ አድርጎ መመለከትም አይቻልም::አገራችን ከዚህ ረጅም የትግል ደብለቀለቀና ውሸንፍር ፊውዳሊዝምንና ኢምፔሪያሊዝምን በሕዝባዊ ሃይል ደምስሳ ብቅ ስትል ለሚፀድቀው ሕዝባዊ ዲሞክራሲያዊ አገዛዝ ጽኑ መሰረትና ተሸካሚ አውታሮች ሆነው ከትግሉ ውስጥ ብቅ የሚሉት እነዚህ አብዮታዊ ማህበራት ናቸው::ባጭሩ ዛሬ የኢትዮጵያን ገጠር በማጥለቀለቅ ላይ ያሉት የገበሬዎች ማህበራት የአድሃሪው ስርአት ቀባሪዎች ብቻ አይደሉም፤ የአዲሲቱ ኢትዮጵያችን ጥንስስ ሃይሎችም ናቸው እንጂ::

ይህንን ለመገንዘብ ብዙም የሚያዳግት አይመስለንም::በመጀመሪያ ደረጃ ልክ በአዋጁ መሰረት መደባዊ ጥራታቸውን ይዘውና አላማቸውን ተከትለው ቢሰሩ እንኳን እነዚህ ማህበራት መሬትን ከባለርስት ነጥቀው ለአራሹ በይዞታ ለመስጠት ሆን ብለው የተደራጁ በመሆናቸው የኢትዮጵያን ፊውዳል ስርአት ጠርሰው ሳይደመስሱ እንደማይገቱ ግልጽ ነው::

ልብ ሳላለው ሰው የማይታየው እነዚህ ማህበራት ለተጠቀሰው አላማ ሲታገሉ ትግሉ ራሱ የሚፈጥራቸውን ሌሎች ትግሎችና አቅጣጫዎች እንደሚወለዱ ነው::በአዋጁ መሰረት ተደራጅተው ሲታገሉ እነዚህ ማህበራት የግድ የአዋጁን ወሰን በጣጥሰው፤ አዋጁ ከሚሰጣቸው መብት አልፈው የአብዮታዊ ሕዝባዊ ስልጣን አውታሮች ለመሆን ይገደዳሉ::ይገደዳሉ የምንለው አውቀን ነው::የኢትዮጵያ ገበሬዎች 'መሬት ላራሹ' በሚለው መፈክር ተሰልፈው ሲታገሉ መሬት ለማግኘት ስልጣንን ከአድሃሪው ስርአት መንጠቅ እንዳለባቸው ይረዱታል::ገበሬዎች በየአካባቢያቸው የሚገኙትን የቀድሞውን ስርአት የመንግስት ስልጣን አውታሮች ሰባብረው ስልጣን እጃቸው ካላስገቡ ትግሉ ወደፊት ሊገፋ እንደማይችል ይረዱታል::ለአድሃሪዎች የሚታዘዘው የመንግስት ስልጣን መኪና ለአዋጁ እንቅፋት ከመሆን አልፎ እነሱ ካላጠፉት እሱ ሊያጠፋቸው እንደሚሞክር፤ እነሱ ካልተኩት እሱ ሊተካቸው እንደሚሞክር በትግል ውስጥ ይማሩታል::

የሌሎችን አብዮቶች ታሪክ ብናይ ሰፊው ገበሬ ለመሬቱ የሚያደርገው ተጋድሎ ዞር ዞር ለነፃነትና ለዲሞክራሲ ከሚያደርገው ተጋድሎ ያልገጠመበት አብዮት የለም::'መሬት ላራሹ' የሚለው መፈክር በርግጥ በስራ ላይ በዋለበት ስፍራ ሁሉ የሕዝቡ ትግል 'ነፃነት ላራሹ' በሚለው መፈክር ስርም ተሰልፎ ታይቶአል::እርግጥ መጀመሪያ ላይ ራሱ ኑሮው:በዝበዛው:ጭቆናው ወጥሮ ይዞታልና፤ የመሬት ጥማት አቃጥሎታልና ሰፊውን ገበሬ ሊያንቀሳቅሰው የሚችለው መሬት ላራሹ የሚለው መፈክር ብቻውን ሊሆን ይችላል::ነገር ግን መሬቱን ከአድሃሪ ሃይሎች ነጥቀ ለመውሰድ የሚደረገው ትግል እያየለ ሲሄድ ሰፊው አርሶ በሌ መሬት የጠማውን ያህል ነፃነትና ዲሞክራሲ ለትግሉ እንደህይወት እስትንፋስ አስፈላጊ መሆናቸውን ይገነዘባል::

ይህ 'ነፃነት ላራሹ' የሚባለው መፈክር ምን ይዘት አለው? ሰፊው ገበሬስ በትግሉ አፍላ ውስጥ የዚህን ነፃነት ጠቃሚነት ተገንዝቦ በዚህ መፈክር ስር ይሰለፋል የሚባለውስ እንዴት ነው?

ታላቁ ሌኒን በመሬት ጉዳይ ሰፊው ገበሬ ያስፈልጉታል ብሎ የገመታቸውን ነፃነቶች በሶስት ክፍሎ የዘረዘራቸው ሲሆን ዋና ዋና ሃሳቦቹ ሲጠቃለሉ እንደሚከተለው ሊታዩ ይቻላሉ:-

1. ሰፊው ሕዝብ ለጋራ ጉዳዩ አስፈላጊ የሆኑትን አስተዳዳሪዎችና የመንግስት ባለስልጣኖች በሙሉ ከሕዝባዊ ምርጫ የማፍለቅ ሙሉ መብት ሊኖረው ይገባል::
2. በሕዝብ ፊት ሃላፊነት የሌለው፤ በሕዝብ ያልተመረጠ፤ ለሕዝብ ተጠያቂ ያልሆነና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሕዝቡ ሊሻር የማይችል መንግስታዊ አስተዳደር ሙሉ በሙሉ መደምሰስ አለበት::
3. አስተዳዳሪዎች በሕዝብ የሚታዘዙ መሆን አለባቸው እንጂ ሕዝቡ የአስተዳዳሪዎች ታዛዥና መሳሪያ መሆን የለበትም::

ከዚህም በማያያዝ ይህንን ነፃነት ሕዝቡ በገዥዎች ወይም ደግሞ በአንዳንድ ግለሰቦች
መልካም ፈቃድ የማያገኘው መሆኑ የታወቀ ስለሆነ 'ነፃነት ላራሹ' የሚለው መፈክር ከስራ ላይ
የሚውለው <u>በሕዝባዊ ጦር</u> ተመርኩዞ እንደሆነ ሌኒን ያስተምረናል::ይህንን ሁሉ ተራማጆች በሙሉ
ያውቃሉ::ሰፊው ገበሬ ግን እነዚህን ሃቆች የሚገነዘባቸው ተራማጆች በሚያደርጉት ቅስቀሳ ብቻ
ሳይሆን ከአድሃሪዎች ጋር በሚያደርገው ተጋድሎ ከሚያገኘው ትምህርትም ነው::

ዛሬ በአገራችን በአይናችን ስር የምናየው ይህንኑ ሃቅ ነው::ሰፊው ገበሬ መሬት ላራሹ
በሚለው መፈክር ተሰልፎ ሲታገል ከአድሃሪዎቹ ጋር ብቻ ሳይሆን ከነርሱም ጋር በሽህ የቆቃም
ከሮች ተሰብስቦ ከተያያዘው የመንግስት መኪና /ስቴት ማሺነሪ/ ጋር ይጋጫል::ይህ ግጭት ትግሉ
በተፋፋመባቸው ቦታዎች ሁሉ የሚታይ ሲሆን አንዳንዱ የጋራ የሆኑ ተጨባጭ መልኮች አሉት::

ግጭቱ በመሰረቱ የሚነሳው የቀደሞው ባለርስት <u>በአዋጁ ላይ በማመፁ</u> ነው::አመፀኛው ባለ
ርስት አዋጁን በማደናቀፍ ወይ መሬቱን አታርሱም:በሬዎን አራጣዎን ብሉ ያስቸግራል፣ አለበለዚ
ያም ምርቱን እንደዱሮው እወስዳለሁ ይላል፤ ባጭሩ እንደቀደሞው እኖራለሁ ብሎ ይነሳል::ተራማጁ
ወገን ይህንን አመፀኛ:ይህንን ህገወጥ ለመንግስቱ ፖሊስ ይጠቁማል፣ ይያዝልን ይላል::ፖሊስ
'የቀን አበል ይከፈለኝ':'ብዙ መሳሪያ ይሰጠኝ'...እያለ ሰበብ ያበዛል፣ እንዲያውም አሁን
በብዙ ቦታዎች እንደሚታየው እነዚህን ፀረሕዝብ ዘራፊዎች ያስተናግዳል::አስተዳዳሪው''ገንዘብ
የለም...በቂ መሳሪያ የለም' ብሎ ነገሩን ይዘጋዋል::ሕዝቡ በራሱ ብቻ መተማመን እንዳለበት
ተገንዝቦ አመፀኛውን በመከራ ከቦ ይይዝና ለፖሊስ ያስረክባል::ፖሊስ ጉቦ በልቶ 'በዋስ ወጣ'
ይለቀዋል::ሕዝቡ ጠላቱን እንደገና ይዞ ራሱ'ወደዳኛ'ይወስደዋል::የመንግስቱ ዳኛም ራሱ ከፍ
ተኛ ባለርስትና በጥቅም የተገዛ መሳሪያ በመሆኑ 'የመሬት ጉዳይ ነውና የማየት መብት የለኝም'
ብሎ ይዘጋል::የገበሬዎች ሸንጎ በአመፀኛው ላይ ይፈርዳል::ግን ሕዝቡ ያሰረውን ፖሊስ መልቦ
ይፈታዋል::ሕዝቡ ጠቅላላውን ከቢሮክራሲውና ከፖሊሱ ሃይለኛ ግጭት ይጀምራል::በዚህ ግጭት መሳ
ሪያ የያዘው አድሃሪው ወገን ስለሆነ ሕዝቡ ይጠቃል፤ በዚህ ሁሉ ማን ወዴት እንደሚያደላ ይገነ
ዘባል::አድሃሪውን ፖሊስ በራሱ ፖሊስ ካልተካ፣ ዳኛውን በዳኛ:ቢሮክራቱን በሕዝባዊ አስተዳዳሪ:
ጦሩን በሕዝባዊ ጦር ካልተካ ሕዝቡ ምንም አይነት መብት እንደማይኖረው ይማራል::ከዚህም አልፎ
የመንግስቱ ፈጥኖ ደራሽ እንደደረሰ ሲደበድበው በመሃከላዊ መንግስት ደረጃም ቢሆን እሱው የመረ
ጠውና በርሱ ድጋፍና ቁጥጥር ስር ብቻ የሚሰራ 'ሕዝባዊ መንግስት' እንደሚያስፈልገው በሚል ፀን
የሚቀጠረው ገበሬ እንደዚህ በትግል ይገነዘባል::

የሕዝቡን ነፃነት ረግጦ ይዞ መሬትን ለአራሹ 'አደላድላለሁ' የሚለው ደርግ የገባበት
ማጥና ሊወጣው የማይችለው ቅራኔ እንግዲህ የሚፈልቀው ከዚህ መሰረታዊ ግጭት ነው::የኢትዮጵያ
አብዮቱ ከንኡስ ከበርቴው ቁጥጥር ስር እንዳይወጣ ስለሚፈልግ ደርጉ ይህንን <u>አብዮታዊ</u> አዋጁ
ከስራ ላይ ለማዋል የሚመክረው በቀደሞው . ስርአት <u>አድሃሪ</u> ቢሮክራሲ ተመርኩዞ ነው::
የጥንቱ ቢሮክራሲ ይህንን አዋጁ
በያለበት እንደሚታየው /ይህ ደግሞ ሊያስደንቀን አይገባም!/
ሙሉ በሙሉ ይቃወማል::ሰፊው ገበሬ ግን ከላይ እንዳየነው ይህንን ሃቅ በእለታዊ ትግሉ የተማረው
በመሆኑ ትግሉን በራሱ ቁጥጥር ስር ማካሄድ እንዳለበት ይገነዘባል::

እንግዲህ ይህ መሰረታዊ ግጭት የደርጉ ሚና ካሁን ወዲያ በኢትዮጵያ አብዮት ውስጥ እየ
ቀነሰ እንደሚሄድና እየቀነሰ መሄድ እንዳለበትም ያበስርልናል::ለደርጉ የሚቀረው ምርጫ ትግሉ
ከቁጥጥሩ ወጥቶ ከሕዝብ እጅ እንዳይገባ ሲፍጨረጨር አዋጁን ማደናቀፍና ከአድሃሪዎቹ ካምፕ ጠቅ
ልሎ መግባትና የነርሱ መሳሪያ መሆን አለበለዚያ ደግሞ ቢሮክራሲያዊው መፍትሄ ጠርሶ እንደማያዋጣ
ተገንዝቦ ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል አለማደናቀፍና ከሕዝቡ መወገን ብቻ ነው::ሌላ አማራጭ
ጉዳና የለውም::

በተራማጆች በኩል ይህ ጉዳይ የደርጉ ውሳኔ የሚጠበቀበት ጉዳይ አይደለም::በያለበት
አዋጁን ከስራ ላይ ለማዋል የሚታገሉት ማህበራት የዚህን የዲሞክራሲ ጉዳይ ዋናነት እንዲገነዘቡት ማገዝ ያስፈልጋል::
ለመሬትና ለነፃነት የሚደረገው ትግል በምንም አይነት ሊነጣጠል ስለማይችል አዋጁን ከስራ ላይ
ስለዚህ በኛ ግምት በአሁኑ ወቅት የተራማጆች ጥረት ራሳቸውን በአገር አቀፍ ደረጃ ማስተሳሰርና

ገጠሩን በሚመለከተው በኩል የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ነው::

1ኛ/ በአዋጁ መሰረት እንደተጀመረው አገሪቱን በገበሬ ማህበራት ማቅለቅለቅ::በአሁኑ ጊዜ ከነቤተሰቦቻቸው ወደ .10 ሚሊዮን የሚጠጉ ገበሬዎች የተደራጁባቸው 12 ሺህ የገበሬ ማህበራት እንዳሉ ይገመታል::ይህ ገበሬዎችን የማደራጀት ጥረት ከግቡ ደረሰ ማለት የሚቻለው 25 ሚሊዮን ገደማ የሚሆኑ ኢትዮጵያውያን በግምት 25 ሺህ ማህበራት ውስጥ ሲደራጁ በመሆኑ በዚህ በኩል የቀረው ተግባር በቀላሉ የሚገመት አይደለም::በተለይ ደግሞ በደቡብና በሰሜን ክፍለሃገራት ያለው መዛባት በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል እስካሁን ድረስ የተቋቋሙት ማህበራት ከቁጥር የሚገቡ እንኳን ሆነው እንዳይገኙ አድርጓቸዋል::ይህ መዛባት ለአብዮቱ የሚያመጣውን ጠንቅ በመረዳት በሰሜን በኩል ያሉትን መሰናክሎች ለመወጣትና በብዛት እነዚህን ማህበራት በማቋቋም ላይ ከፍተኛ ጥረት መደረግ ይኖርበታል::

እርግጥ ነው፣ እነዚህ ማህበራት እንዳይቋቋሙ አድሃሪዎች የማይጠነስሱት ሴራ የላቸውም:: ዘማቾችንና ተራማጅ አስተዳዳሪዎችን ከሕዝቡ ለመነጠል የፈጠራ ወሬ ይነዛሉ፣ ተራማጅ ዘማቾችን ያስራሉ:ያባርራሉ:ይገድላሉ፣ አንዳንድ ዘመቻ ጣቢያዎችን ከነጥራሹ ይዘጋሉ፣ ተራማጅ አስተዳዳሪዎችን ያስፈራራሉ:ያነሳሉ፣ የገበሬ ማህበር መሪዎችን አለምክንያት በፖሊስ ጣቢያው ያስራሉ:: ይህ ሁሉ አለባካ ባሉ ማህበራት ቢቋቋሙ ስልጣናቸውን ለመቀነስ ከአድሃሪው ቢሮክራሲ ጋር ተጣብቀው ያሴራሉ::

ለጊዜው የገበሬዎች ማህበራት ውሱንነት /ከአውራጃ ደረጃ አያልፉም፣ የሚታዘዛቸው ፖሊስና ጦር ሰራዊት የላቸውም፣ የወሰኑትንና የፈረዱትን ማስፈፀሚያ ስልጣን የላቸውም.../ አንዳንዶችን ተስፋ ሊያስቆርጥ ይችላል::ግን ይህ በፍፁም የገበሬ ማህበራትን አብዮታዊ ሚና ሊያስተን አይገባም::እንደዚህ ተወስነውም ቢሆን የገበሬዎች ማህበራት በአገራችን ያብቡ::ይህ የዛሬው ውሱንነታቸው ራሱ ገና ከመጠንሰሳቸው ከአድሃሪው ስርአት የስልጣን አውታሮች ጋር ስለሚያጋጫቸው የወደፊቱን የትግል አቅጣጫ የሚያመለክት ቀስት ነው::

2ኛ/ ዛሬ /ገና ደግሞ ለጥቂት ጊዜ/ ይህን አዋጅ ስላወጀ ብቻ ደርጉ ከስራ ላይ ያውለዋል የሚል የተሳሳተ እምነት በሰፊው ሕዝብ ዘንድ ይታያል::የዚህ እምነት ፋርሽነት በተግባር ይገለጣል::በሚሊዮን የሚቆጠሩ ገበሬዎች በየእለቱ በየመንደሩ:በየጥቃቅኑ አጋጣሚ ከአድሃሪዎቹ እንቀፋትነትና ከደርጉ ተባባሪነት ወይም ወላዋይነት በሚያገኙት ትምህርት መተማመን የሚቻለው በሕዝቡ ትግልና በሕዝቡ ስልጣን ላይ ብቻ መሆኑን ይረዱታል::ተራማጆችን ካሁኑ የሚጠብቀን የግንባር ቀደም ተግባራችን ከጠበቡ አለታዊና ጥቃቅን ግጭቶች እየተነሳን የቀስቀሳው ተግባር በዚህ እየተፋፋመ በሚሄደው የመንግስት ስልጣን ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር ማድረግ ነው::

3ኛ/ በቀበሌ ደረጃ ሕዝቡ በትግል ስልጣኑን ከእጁ ማስገባት ቢችል እንኳን መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላቶቹን ደምስሶ የራሱን ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አገዛዝ /ዲክቴተርሽን/ በአገር አቀፍ ደረጃ እስከመሰርት ድረስ የተበታተነ ድል ምንም አይነት ቋሚ ዋስትና እንደሌለው መረዳት ይገባል::ስለዚህም እስከአገርአቀፍ ደረጃ የተሳሰሩትን አድሃሪዎች በመቋቋም ሰፊው አርሶአደር በዚሁ አኳያ የግድ መደራጀት እንዳለበት አንረሳም::በተጨማሪም ይህ አገርአቀፍ ትግል ከሌሎች አብዮታዊ ሃይሎች/በተለይ ደግሞ ከወዝአደሩ/ ጋር ትብብርና አንድነትን የሚጠይቅ መሆኑን ተገንዝቦ የባላገሩ ትግል በከተማ ከሚደረገው ትግል ጋር የሚቀነባበርበትን ዘዴ መሻትና በሰው አቅጣጫ:በሰው መንፈስ ገበሬዎችን ማስተማር ያስፈልገዋል::

××××××

## II

ዛሬ የኢትዮጵያ አብዮት በማጥለቅለቅ ላይ ያለው ገጠሩን እንደሆነና የመሬቱ አዋጅ የኢትዮጵያን ገጠር /በተለይ ደግሞ የደቡብንና የምስራቅን ክፍለአገራት/ ታላቅ አብዮታዊ ማእበል ውስጥ እንደጨመረው ግልጽ ነው:: ከተሞች በዚህ ትግል ውስጥ የራሳቸው የሆነ የትግል ቁተር እንዳላቸው ግልጽ ቢሆንም እነርሱ በገጠሩ: ገጠሩ ደግሞ መልሶ በነርሱ ላይ ታላቅ ተጽእኖ እንዳለው አይካድም::

የሰፊው ሕዝብ የትግል ማእበል እያስበረገጋቸው የሚሸፍቱት: ገጠሩን እየለቀቁ በከተሞች የሚከማቹትና የሚደራጁት አድሃሪያች ስፍር ቁጥር የላቸውም:: በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች በአሁኑ ጊዜ ገጠሩ ለአብዮት እጅግ ያመቸውን ያህል በከተሞች ደግሞ አብዮቱ ለአድሃሪያች ደረቱን ገልጦ የሰጠ ነው ለማለት ይቻላል::

በከተማ ያለውም ትግል ቢሆን የባላገሩን ያህል ቁርጥ ያለና የተጣራ መልክ አይኑረው እንጂ አሁንም በመፋፋም ላይ መሆኑ ግልጽ ነው:: በወዝአደሩ በኩል ኢሰአማ በደርጉ የተሰነዘረበትን ጣልቃገብነት ሙሉ በሙሉ አክሽፎ ድርጅቱን መልሶ አቋቁሟል:: የተወረሱት ፋብሪካዎችና ልዩ ልዩ ድርጅቶች 'የሕዝብ' ተባሉ እንጂ እስካሁን ድረስ የሃብቱ ፈጣሪ የሆነው ወዝአደር ከዚህ ወረሳ ያገኘው ትርፍ እያቆለቆለ የሚሄድ የኑሮ ደረጃ ብቻ ነው:: በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኑሮ ዋጋ ወደሰማይ እየመጠቀ ሲሄድ አንድም የደመወዝ ጭማሪ በመነፈጉ ወዝአደሩ መኖር ከማይችልበት ሁኔታ ላይ ወድቆ ይገኛል:: የአስተማሪዎቹም ጥያቄ የረባ መልስ ሳያገኝ በ'ይታይላችኋል' ብቻ አመት ከመንፈቅ ሙሉ ፍጭ ብለዋል:: የደርጉ ፈጽሞ ያልተጣራና የተወናበደ ፖለቲካ ትንንሽ ነጋዴዎችን ምንም አይነት የህልውና ዋስትና ስለነሳቸው የንግድ እንቅስቃሴ በጣም ተዳክሞአል:: በየቦታው የሚሰማው እሮሮ ብቻ ነው:: ያገሪቱ ኢኮኖሚ እያዘቀጠ በመሄድ ላይ ይገኛል:: በዚህ ላይ የኢምፔሪያሊስቶች: የአቀባባይ ከበርቴዎች: የቢሮ ከበርቴዎች ወዘተ. ሳቦታጅ ከቀን ቀን እየተቀነባበረ በመሄዱ አገሪቱ ወደትልቅ የኢኮኖሚ ክሪስ በማምራት ላይ ተገኛለች::

ይህንን ሁሉ የሚያባብስ ደግሞ የተወዛገበ የፖለቲካ ሁኔታ አለ:: የአብዮቱ ወዳጆችና ጠላቶች በቅጡ አልተለዩም:: ወላዋይና መሃል ሰፋሪ የሆኑት ሃይሎች ወደአድሃሪው ወገን እየተደበለቁ ናቸው:: ቁርጠኛ የሆኑት ጠላቶች እየተደራጁና ትግላቸውን እያስተባበሩ ናቸው:: ወዝአደሩ ተደራጅቶና አርሶአደሩን አስከትሎ አመራሩን ባልጨበጠበትና ተራማጁ ወገን እንደዚህ ተራቁቶና ተበታትኖ በሚገኝበት በአሁኑ ሰአት አብዮቱ በተለይ በከተሞች ከፍተኛ አደጋ ላይ እንደሆነ ግልጽ ነው::

ይህንን አደጋ ጠንቅቀው በመመልከት የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ: የአድሃሪያችን ሴራ ለማክሸፍና አብዮቱን ወደፊት ለመግፋት የኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ በአዋጅ የተነጠቃቸውን ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቹን እንዲጎናፀፍ ከጐኑ ተሰልፈው ጠንክረው መዋጋት አለባቸው:: በአሁኑ ጊዜ ከስልጣን ኮርቻ ላይ ቁብ ካለውና በመደባዊ ጥቅሙ ታውር እውነቱን አላይ ካለው የንኡስ ከበርቴ ፀረዲሞክራቲክ ክንፍ በስተቀር ዲሞክራሲ ለሕዝቡ ትግል የህይወት እስትንፋስ መሆኑን ያልተገነዘበ ተራማጅ የህብረተሰብ ክፍል የለም:: እንደዚህም ስለሆነ የመጣ 'መከራከሪያ' ቢመጣ ይህንን ሃቅ ሊሸፍንብን ስለማይችል: በዚህ በኩል የሚደረገው ትግል ዘር ዘር በተራማጆችና በአድሃሪያች መካከል የሚደረግ ትግል ሆኖ መታየት አለበት::

ፀረዲሞክራሲያዊው ደርግ መላው ተራማጅ በዚህ ጥያቄ ላይ ተነሳስቶ ወጥሮ ስለያዘው 'ዲሞክራሲን የከለከልኩት ቢታወጅ ከሕዝቡ ይልቅ ለአድሃሪያች ይረዳል ብዬ በመፍራት ነው' የሚል ተለካሻ ሰበብ ይሰጣል:: የኢትዮጵያ ተራማጆች ደግሞ በአንድ ድምጽ በፊትም አሁንም የአድሃሪያችን ቀስም ለመስበር፤ ሴራቸውን ለማክሸፍ፤ አወናባጅ 'ተራማጆችን' ለማጋለጥ፤ የቀበሮ ባህታውያንን ከሕዝቡ ለመነጠል፤ የትግሉ ባለቤት የሆነውን ሰፊውን ሕዝብ ለማደራጀት የግድ እነዚህ እነዚህ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያስፈልጉናል ይላሉ::

መቸስ ይህ ዲሞክራሲ ከስራ ላይ ቢውል አድሃሪያችን ያግዘብናል የሚለው ሰበብ በሕዝብ ንቀት የተበከለ: ራሱ አድሃሪ የሆነ አስተሳሰብ ብቻ ሳይሆን የማንኛውም አብዮት ሆነ የጊዜው የኢትዮጵያ ሁኔታ የሚያስተባብለው ከንቱ ማወናበጃ ነው:: አድሃሪያች አንድን ሕዝብ ረግጠው

ለሙገዛት የትና መቼ ነው ዴሞክራሲያዊ መብቶች አስፈልገዋቸው የሚያውቁት? አሁንስ ቢሆን እፍኝ የማይሞሉ አመፀኛ ባለርስቶች በያለበት ዘማችና ተራማጅ አስተዳዳሪዎቻችን፡ድሃ ገበሬዎቻችን የሚያስሩትና የሚረሽኑት በሚልዮን የሚቆጠረው ሕዝብ ዴሞክራሲያዊ መብቱን ተነፍጉ ለነሱ ስለተመቻቸው አይደለም ወይ?

የመደራጀት መብት ከተፈቀደ አድሃሪዎችም ይደራጃሉ የሚል ሌላ ማወናበጃ አለ፡፡እዚህስ ላይ አድሃሪዎች ለመደራጀትና ጥቅማቸውን ለማስተሳሰር መቼ ነው ዴሞክራሲ አስፈለጉአቸው የሚያውቁት? እስከዛሬስ ተደራጅተው ሲረግጡን ለዘመናት የቆዩት በየትኛው ዴሞክራሲ ተጠቅመው ነው? ትናንት ሙሉ በሙሉ በመንግስት ደረጃ ተደራጅተው አልነበረም? ዛሬስ አድሃሪው የመንግስት ቢሮክራሲ መቼ ተነካ? ተበታትነዋል ቢባልስ ዴሞክራሲ ታፍኖ እስከተያዘ ድረስ ከሕዝቡ ቀድመው እንደሚደራጁ ለማየት እንዴት አዳጋች ይሆናል?

የዴሞክራሲ መጥፋት አድሃሪዎችን በምንም አይነት ከመደራጀት አያግዳቸውም፡፡መጀመሪያ ነገር በሚልዮን ከሚቆጠረው ሰፊ ሕዝብ ጋር ሲወዳደሩ እጅግ በጣም ጥቂት ከመሆናቸው ሌላ በተለይ ቀንደኞቹ ከድሮውም የሚተዋወቁና በጥቅም የተሳሰሩ ናቸው፡፡በተጨማሪ ደግሞ አብዮት በሚፋፋምበት ጊዜ 'አግኝተው ያጡና' ጥቅማቸውን ጠንቅቀው የሚያውቁ በመሆናቸው በእንደዚህ አይነቱ ጊዜ አብዮትን ለመቋቋም በፖለቲካና በድርጅት በኩል የሚያሳዩትን ጥረት እጥፍ ድርብ ያደርጉታል፡፡በዚህ ላይ የገንዘብ ሃይል አላቸው፡፡በህብረተሰቡ ውስጥ ያንሰራራውና ገና በቅጡ ያልተመታው /ዴሞክራሲ ባለመኖሩ/ የነርሱው ርእዮተአለም ነው፡፡ገና ያልተሰበረው /አሁንም ዴሞክራሲ ባለመኖሩ!/ የነርሱው ታዛዥ ቢሮክራሲ ነው፡፡ይህንን ሁሉ ስናይ የዴሞክራሲ መጥፋት አድሃሪዎችን የሚያግዝ መሆኑን እንገነዘባለን ማለት ነው፡፡

ደርጉ ይህ እንደማያዋጣው ተገንዝቦ ሌላ ያገኘው የንኡስ ከበርቴ ሴራ ከዚህ በፊት እንዳልነው አንድ 'ተራማጅ ድርጅት' አቋቁሞ የሕዝቡን ትግል ለመግታት የሚያደርገው ሙከራ ነው፡፡ከዚህ በፊት በሰጠነው ትንተና /ሰ.ሕ.ድ. ቁጥር 24/ ይህ 'ተራማጅ ድርጅት' የሆነውን ቢሆን ዴሞክራሲ በስራ ላይ ሳይውል ከላይ ቢወረወርልን የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ያው እንደአገር አስተዳደር፡እንደፍርድ፡እንደገንዘብ ሚኒስቴር... የመንግስት ተቀጥላ የሆነ መስሪያ ቤት እንጂ ሌላ ነገር አድርገን አንወስደውም፡፡በእንደዚህ አይነቱ 'ተራማጅ' ድርጅት መታወጅ፡በኢትዮጵያ ዴሞክራሲ ሰፈነ ብሎ የሚያጨበጭብ አይገኝም፡፡እንዲያውም እንዲህ አይነቱ ድርጅት ሕዝቡ ለዴሞክራሲያዊ መብቶቹ የሚያደርገውን ትግል የሚያወናብድ የንኡስ ከበርቴዎች ሴራ በመሆኑ መላው የኢትዮጵያ ተራማጆች አጥብቀው ይዋጉታል፡፡

በዚህ ጉዳይ ሁለት ነገሮችን መጨመር እንወዳለን፡፡ተራማጆች አንድ ፓርቲ የሚለውን የንኡስ ከበርቴዎች ፈሊጥ አይቀበሉትም፡፡ፓርቲ ማለት የአንድ መደብ ንቁና ግንባር ቀደም ግለሰቦች በመደባዊ አላማ ተደራጅተው የዚያን መደብ ጥቅም ለማስከበር የሚቆሙበት መደባዊ ቡድን ማለት ነው፡፡ግንባር ማለት የተለያዩ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች ለአንድ ለተወሰነ የጋራ አላማ ድርጅታዊ ነፃነታቸውን እንደጠበቁ ሆነው በጋራ ጠላት ላይ ትግላቸውን የሚያስተባብሩበት የድርጅቶች ድርጅት ማለት ነው፡፡

እንግዲህ እንዲህ ከሆነ አንዳንድ ሃቆች ግልጽ ሆነው ይታያሉ፡፡በአገራችን የሚካሄደው ትግል ፀረፊውዳልና ፀረኢምፔሪያሊስት ሲሆን ትግሉ ከግቡ እንዲደርስ ከተፈለገ የተለያዩ መደቦችና የህብረተሰብ ክፍሎች /90 በመቶ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያቀፉ/ በቀድሚያ ራሳቸውን በፓርቲ መልክ አደራጅተው በግንባር መልክ ትግላቸውን ማስተባበር አለባቸው፡፡ስለዚህ ሕዝቡ በልዩ ልዩ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተደራጅቶ በሙሉ ልቡ የማይሳተፍበትና የማያስተሳስርበት ድርጅት ትግሉን ከግቡ ሊያደርሰው አይችልም፡፡ደርጉ እንግዲህ አቋቁማለሁ የሚለውን 'ተራማጅ' ድርጅት የሰጠውን ስም ቢሰጠው የሕዝቡን ትግል ለማፈን የሚሞክሩ የንኡስ ከበርቴ ግለሰቦች ጥርቅም እንጂ ከዚህ አልፎ የሚሄድ አይደለም፡፡

ይህ 'ተራማጅ' ድርጅት ፓርቲ ነኝ ብሎ ቢቀርብ ከህብረተሰቡ መደቦች ሊወክል የሚችለው የንኡስ ከበርቴውን መደብ ፀረዴሞክራሲያዊ ክንፍ ብቻ ነው፡፡ግንባር ነኝ ብሎ ቢቀርብ፡አስቀድመው በዴሞክራሲ ተደራጅተው ፕሮግራማቸውን የጋራ ከሆነው ሕዝባዊ ፕሮግራም አስተያይተው፡ተወያይ

ተውና ፈቅደው በሙሉ ልብ የገቡበት ፓርቲያችና ሌሎችም ድርጅቶች ስለሌሉበት ቀፎ 'ግንባር' ነው ማለት ነው::እንደዚህም ስለሆነ አሁንም ቢሆን ይህ 'ግንባር' በኢትዮጵያ አብዮት ላይ ከሚያሴሩ ፀረ ዲሞክራቲክ ንኡስ ከበርቴ ግለሰቦች አለፍ አይሄድም::

ደርጉ አሁንም እውነተኛውን ዲሞክራሲ ለማድበስበስ ይህ የማይጠቅመው ድርጅት የተለያዩ የሙያና የሰፊ ሕዝብ ድርጅቶችን የያዘ 'ግንባር' ይሆናል ይላል::በዚህም የሚወናበድ ተራማጅ አይገኝም::እርግጥ የተባሉት የሙያና የሰፊው ሕዝብ ድርጅቶች ከዚህ 'ግንባር' ውስጥ ሊገቡ ይችላሉ::ነገር ግን የሙያ ድርጅቶች አባሎችና አመራሩንም የሚይዙት ግለሰቦች የሚመረጡት እስከዚህም በፖለቲካ አቋማቸው ሳይሆን ለሙያቸው ወይም ላሉበት ሌላ ድርጅት እድገት በሚያሳዩት ትግልና ታታሪነት ነው::አንድ የሙያ ማህበር ውስጥ /ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሃኪሞች ማህበር/ አድሃሪም ተራማጅም ወላዋይም አባል ሊሆኑ ይችላሉ::ስለዚህ ሃኪሞች ሙያቸውን በሚመለከተው በኩል እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ በአንድ የሙያ ድርጅት ውስጥ መታገል ቢችሉም ቀጥታ ፖለቲካን በሚመለከተው በኩል የተለያዩ የፖለቲካ ፓርቲያች አባል ይሆናሉ::ስለዚህ የፖለቲካ ፓርቲያች ሳይኖሩበት በሙያና የሰፊ ሕዝብ ድርጅቶች ብቻ የተቋቋመ ግንባር የራሱ የሆነ የተጣራ የፖለቲካ አቋም ስለማይኖረው በዚህ በኩል በቀጥታ በመንግስቱ /ማለት በንኡስ ከበርቴው/ የፖለቲካ አመራር ስር ይወድቃል ማለት ነው::

ይህንን እንኳን ይሁን ብለን ይህ 'ግንባር' በነዚህ ድርጅቶች ብቻ ተቋቋመ ቢባልም በዚህ ደረጃ እንኳን ደርጉ የዲሞክራሲን ጥያቄ ሊያመልጠው አይችልም::ምክንያቱም ሁለተኛው ቁምነገር ይህ 'ግንባር' በውስጡ የፖለቲካ ፓርቲያች ያስፈልጉታል ብቻ ሳይሆን ያቀፋቸው ድርጅቶች በሙሉ አሰራራቸው በዲሞክራሲ ካልሆነ ሰፊውን ሕዝብ ያቀፈና ሰፊው ሕዝብ መልሶ ያቀፈው 'ግንባር' ሊሆን አይችልም::'ግንባር' ያስፈልጋል የሚባለው የሰፊውን ሕዝብ የተለያዩ ክፍሎች በአንድ የጋራ አላማ ላይ አንቀሳቅሶ ለማታገል ነው::ይህን የጋራ አላማ ሕዝቡ እንዲቀሰቀስበትና ስራ ላይ ለማዋልም አስፈላጊውን መስዋእትነት ለመቀበል ዝግጁ እንዲሆን ከተፈለገ ከሰፊው ሕዝብ ፍላጎት የመነጨ አላማ መሆን ይገባዋል::ስለዚህ እነዚህ ድርጅቶች የግንባሩ አባል ከመሆናቸው በፊት እንወክላለን የሚሉትን ክፍል ፍላጎትና አላማ የሚያንፀባርቁ ዲሞክራሲያዊ ድርጅቶች መሆን አለባቸው ማለት ነው::ለዚህ ደግሞ የግድ በዲሞክራሲ መወያየት:መወሰን:መሪዎችን መምረጥ:አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ደግሞ መሻር የሚቻልበት አካባቢ መፈጠር አለበት ማለት ነው::

ይህ ካልሆነ እነዚህ ድርጅቶች ሕዝቡን በምንም አይነት አይወክሉም ማለት ነው::ሕዝቡን ለትግሉ ማንቀሳቀስም አይችሉም ማለት ነው::እንደዚህ ከሆነ ደግሞ ይህ 'ግንባር' ድርጅቶችን አቅፌያለሁ ብሎ ለማወናበድ ቢሞክር በአባልነት የሚይዛቸው ሰዎች ከራሳቸው በስተቀር ማንንም የማይወክሉ ግለሰቦች ብቻ መሆናቸው ግልጽ ነው::

የኢትዮጵያን አብዮት ሰፊው ሕዝብ እንጂ ፀረ ዲሞክራቲክ ግለሰቦች ከስራ ላይ እንደማያውሉት ግልጽ ነው::በዲሞክራሲያዊ አሰራር ተመርኩዞ:በወዝአደሩ አመራር ስር ተሰልፎ:በአንድ አብዮታዊ ሕዝባዊ ግንባር እስካልተሰለፈ ድረስ የኢትዮጵያ አብዮት ከግቡ አይደርስም::ይህንን በመረዳት በዲሞክራሲው ግንባር ትግላቸውን ማፋፋም የያዙት ተራማጆች በሙሉ በኛ ግምት የሚከተሉትን ርምጃዎች ባስቸኳይ መውሰድ ይኖርባቸዋል:-

1. ለዲሞክራሲ መብቶች ሲታገሉ የቆዩ የሙያ ማህበሮች:የሰፊ ሕዝብ ድርጅቶችና ተራማጅ የህብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ ለዲሞክራሲ በሚያደርጉት ትግል ከውሳኔ አልፈው በተግባር በአንድነት የሚሰለፉበትን ዘዴ ተገናኝተው ማጥናት አለባቸው::

2. በዚህ በዲሞክራሲ ጥያቄ ላይ ምንም አይነት ማወናበድ እንዳይኖር፣ የሚቀርቡት ጥያቄዎች የመደራጀት:የመፃፍ:የመሰብሰብ ... የመሳሰሉትን ሰብአዊ መብቶች ያለአንዳች ገደብ እንዲታወጁ ለማድረግ መታገል ያስፈልጋል::

ትግላችን በገጠርም ሆነ በከተማ በዚህ አግባቢ ከተቀናበረ የኢትዮጵያ አብዮት ከመታፈን አልፎ አዲስ አስተንፋስ:አዲስ ጉልበት እንደሚያገኝ አንጠራጠርም::ባላገሩ በአብዮቱ መጥለቅለቁን ይቀጥላል::የአድሃሪዎች ምሽግና የሴራ መጠንሰሻ ዋሻ መሆን በጀመረት ከተማዎች ትግሉ እንዳይታፈንና አድሃሪዎችን መድረሻ ለማሳጣት በዲሞክራሲ ግንባር የሚካሄደው ትግል መግፋት አለበት::ከእንግዲህ ሰማይ ዝቅ ምድር ከፍ ቢል በምንም ሃይል ሊገታ የማይቻለውን የኢትዮጵያን አብዮት ባለቤት ገርቼ እይዛለሁ የሚለው የንኡስ ከበርቴው ደርግ አቋም በመሰረቱ ለአብዮቱ ሳይሆን ለአድሃሪ ሃይሎች የሴራ መጠንሰሻ ፋታ የሚሰጥ አቋም መሆኑ ግልጽ መሆን አለበት::እንደዚህም ስለሆነ ራሱ አድሃሪ አቋም በመሆኑ የኢትዮጵያ ተራማጆች በሙሉ ሃይላቸውን አስተባብረው ይዋጉታል::

አብዮታዊ የገበሬ ማህበራት ያብቡ !

የሰፊው ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ መብቶች ትግል ይግፋ !

ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያሊዝም ይወድማሉ::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ያሸንፋል::